# <u>ዶግማ (እምነት) እና፡ ቀኖና</u>

# <u>ክፍል ፩</u>

## <u>ዶግማ (ትምህርተ ሃይማኖት)</u>

<u>፩. ሁሉን በያዘ፥ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።</u>

ሀ. «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ»። ......................................ዘጸ 20፥3

ለ. «እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ፥በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና»። ..................ዘጸ 20፥11

ሐ. «እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ፥በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ፥ ሌላም አምላክ እንደሌለ ዛሬ እወቅ»። ..................................ዘዳ 4፥39

መ. «እስራኤል ሆይ ስማ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው»። ..................................................ዘዳ 6፥4

ሠ. «ለእኛስ ነገር ሁሉ፥ከእርሱ የሆነ፥ እኛም ለእርሱ የሆንን፥አንድ አምላክ አብ አለን»። ..................................፩_ቆሮ 8፥6

ረ. «ከሁሉ በላይ የሚሆን፥በሁሉም የሚሠራ፥ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ፥ የሁሉ አባት አለ»። ..................................ኤፌ 4፥6

<u>፪. ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ፥የአብ አንድ ልጁ በሚሆን፥በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።</u>

ሀ. «እግዚአብሔር አለኝ፥አንተ ልጄ ነህ፣ እኔም ዛሬ ወለድኩህ»። .......እብ 1፥5

ለ. «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ»። ..................................መዝ 109፥3

ሐ. «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ፥እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና»። ..................................................ዮሐ 3፥16

መ. «በጌታ በኢሱስ ክርስቶስ እመን፥ አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ»። ..................................................የሐዋ 16፥31

ሠ. «ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ፣ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን። አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን»። ..........፩ ቆሮ 8፥6

ረ. «ይህም በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ፣ ለኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው»። ..................................ፊል 2፥10

<u>፫. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፣ የተወለደ እንጅ፥ ያልተፈጠረ፣ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል።</u>

ሀ. «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ቃልም እግዚአብሔር ነበረ»። ..................................................<u>ዮሐ 1፥1</u>

ለ. «እኔና አብ አንድ ነን»። ..................................................<u>ዮሐ 10፥30</u>

ሐ. «እኔን ያየ አብን አይቶአል»። ..................................................<u>ዮሐ 14፥9</u>

መ. «ለአብ ያለው ሁሉ፥ለእኔ ነው»። ..................................................ዮሐ 16፥15

ሠ. «ከአብ ወጥቼ፥ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፣

ሸ. «ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው።
እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት»።..............................................................፩ ቆሮ 15፥14

**<u>፯. በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፣
ዳግመኛም በጌትነት ይመጣል።ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።</u>**

ሀ. «ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ፣ ወደ ሰማይም ዐረገ»።..................ሉቃ 24፥51
ለ. «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደሰማይ የወጣ ማንም
የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው»።.........................ዮሐ 3፥13
ሐ. «ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፣
ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው»።........................................የሐዋ 1፥9
መ. «እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ
ሳሉ፥እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፣
ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ
ስለምን ቆማችኋል?ይህ ከእናንተ የወጣው ኢየሱስ፥
ወደ ሰማይ ሲሄድ እንደአያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው»።..................የሐዋ 1፥10
ሠ. «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም፥
በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ»።..........................................የሐዋ 7፥55
ረ. «በሌሊት ራእይ አየሁ፥እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል
ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፥በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፥
ወደ ፊቱም አቀረቡት፥ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም
የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው።
ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፣መንግሥቱም የማይጠፋ ነው»።...........ዳን 7፥13
ሰ. «በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፣
ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም»።..............................................ሉቃ 1፥33
ሸ. «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ
አለውና፣ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል»።...........................ማቴ 16፥27
ቀ. «ጌታ ራሱ በትእዛዝ፥በመላእክትም አለቃ ድምፅ፥
በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና»።..............................፩ ተሰ 4፥16

**<u>፰. በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፣ ጌታ፥አዳኝ በሆነ፥
ከአብ በሠረፀ፥ እንስገድለት እናመስግነውም፥ ከአብና ከወልድ
ጋር፥በነቢያት የተናገረ፣</u>**

ሀ. «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድና
በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ
እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው»።.....................ማቴ 28፥19
ለ. «ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ጌታ ጌታየን ጠላቶችህን».......................ማር 12፥36
ሐ. «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፥
እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ
ስለእኔ ይመሰክራል»።..........................................................ዮሐ 15፥26
መ. «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥
ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች
በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ»።..............................................፪ ጴጥ 1፥21

